# የአሲምባ የውይይት መድረክና የጠላት አፈራረጅ

ቅዳሜ (July 27/2008) ዓም በአሲምባ የውይይት መድረክ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶችን በተመለከተ ሰፊ ውይይት ተደርጎ ውሏል ። ርእሱ በጣም ሰፊና ረጅም የውይይት ጊዜን የጠየቀ ነበር ። ሆኖም ግን እኔ እጅግ አጠር ባለ መልኩ በዚህ ጽሁፍ ከመድረኩ የቀሰምኩትን የተቻለኝን ያክል በምችለው ውሱን ቋንቋ ለማቅረብ እንጂ የክፍሉ ታዳሚዎች እንደተወያዩበት የጠለቀ ግንዛቤ ለማስያዝ ብቃቱም ስለሌለኝ አቅም በፈቀደ ይህን ትምህርታዊ ውይይት ለአንባቢያን በመጠኑ ለማድረስ እንደሆነ በቅድሚያ አሳውቃለሁ ።

በመጀመሪያ <u>“ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ነው”</u> በሚለው የመድረኩ ታዳሚ በሙሉ አለአንዳች ማወላዳት የተስማማበት ስለሆነ በዚያ ላይ ብዙም የምለው አይኖረኝም ። ዋናውና አከራካሪው ነጥብ የነበረው ግን ወያኔን የሚቃወሙ ሌሎች ድርጅቶች የሕዝብ ወገን ናቸው ወይ? ወይንስ አንዳንዶቹ ከሕዝብ ወገንነት የማይመደቡ እንዲያውም በጠላትነት ሊፈረጁ የሚገባቸው ናቸው የሚለው ነጥብ ነበር ውይይቱን ሰፊ ግዜ የወሰደው ።

የተቃዋሚ ቡድኖችንም እኔ እስከገባኝ ድረስ በሶስት ደረጃ በመክፈል ነበር  የተመለከቷቸው ፤ አመዳደባቸውም ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው ይሆናል ።

፩ኛ-ግንጠላን የሚያቀነቅኑ ኢትዮጵያዊነትን የማይቀበሉ እንደ ኦነግና ፣ ኦብነግ ያሉትን ።

፪ኛ- ከቅንጅት ፣ ከሕብረት ፣ እንዲሁም ከኢሕአፓ ተገንጥለው የወጡና ከወያኔ ጋር ለመስራት ፍላጎት ያላቸው ።

፫ኛ- ደረጃ ደግሞ አለአንዳች ማመንታትና ማወላዳት ወያኔ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ሕዝብ ስለሆነ በማናቸውም ሁኔታ ከስልጣን መወገድ አለበት ፤ በምንም አይነት ደረጃ ይሁን ከወያኔ ጋር አብሮ መስራት አይቻልም በሚለው ቡድን ነበር ።

በመጀመሪያ ግንጠላን በማቀንቀን ወያኔን የሚቃወሙትን በተመለከተ ስለ አደገኛነታቸው በሰፊው ከተወያዩ በኋላ ያነሱትንም የብሄርና የግንጠላ ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለውና የሚያነሱትም የብሄር ጭቆና ጥያቄ ሊፈታ የሚችለው የግለሰብ መብት ሲከበር እንጂ እነሱ እንደሚያቀነቅኑት የወል መብት እንዳልሆነ በማስረገጥ ቢቻል የያዙትን አላማ እንዲያስወግዱ ጥረት በማድረግ ፣ በማስተማር ወደ ሕዝብ ወገን እንዲቀላቀሉ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ በመተማመን አያይዞም ይህንን ሕዝባዊ ጥሪ ችላ ብለው የያዙትን የግንጠላ ከበሮ የሚደልቁ ከሆነ ግን ያው ወደ ጸረ ሕዝብነት ተመድበው በጠላትነት መፈረጅ የግድ መሆኑን አስገንዝበዋል ።

እዚህ ላይ በጠላትነት የተፈረጁት በሙሉ የአፈራረጃቸው ደረጃና ቅደም ተከተልም ሊኖረው እንደሚገባ በሰፊው ውይይት የተካሄደበት ሲሆን ፣ ምንም እንኳ በሕዝብና በሐገር ጠላትነት ቢፈረጁም እንደ ዋነኛ ጠላታችን ወያኔ መመታትና መደምሰስ አለባቸው በሚል ሳይሆን ሕብረተስብን በማንቃትና በማስተማር ተቀባይነት እንዳይኖራቸው በማድረግ ፤ ነገር ግን ከሕዝብ ፍላጎት ውጪ አላማቸውን በማራመድ እኛ እንደፈቀድን እናደርጋለን ካሉ ግን ያው መገለል እንደሚኖርባቸው ሆኖም ግን ለጊዜው እራሳቸው ተሳዳጅና ስልጣን ላይ ሆነው በቀጥታ

በሕብረተሰቡ ላይ እንደ ወያኔ በደል ሰለማያደርሱ ጠላትነታቸው ከወያኔ ዝቅ ባለ ደረጃ ተፈርጆ ግን የሕዝብ ጠላትነታቸው አጠያያቂ እንዳልሆነ አስምረውበት አልፈዋል ።

በሁለተኛ ደረጃ የተመለከቷቸው ደግሞ ከቅንጅት ፣ ከሕብረትና ከኢሕአፓ አፈንግጠው በመውጣት እራሳቸውን የወያኔ ተቃዋሚ ብለው የሚጠሩትን ነገር ግን ባብዛኛው ታዳሚ ለወያኔ ያጎበደዱ ወይንም ወያኔ እንዲቀበላቸው የመለሳለስና የመለማመጥ አዝማሚያ ያላቸው በማለት በሐገር ውስጥም ሆነ ከሐገር ውጪ ሆነው የሚንቀሳቀሱትን የተቃዋሚ ቡድኖችን ነበር ።

ይሄኛው የውይይት አርዕስት ነበር እንደ አወዛጋቢ የታየውና አብዛኛውን የውይይት ጊዚያቸውን የወሰደው ሆኖም ግን በስተመጨረሻው በአንድ ድምጽ ስምምነት ላይ ባይደረስም ነገር ግን ሁሉም የትግሉ እንቅፋቶች በመሆናቸው ላይ አስምረውበታል አልፈዋል ፤ ስለሆነም ርዕሱን ለመጨረስ በቂ ጊዜ ባለመኖሩ የተነሳ ሙሉ ስምምነት ላይ መድረስ ስላልተቻለ በይደር ለሌላ የውይይት ጊዜ ተላልፎ ክፍሉ ተዘግቷል ።

በመድረኩ እጅግ በጣም ሰፊ በሆነና ከአገራችንም ሆነ ከውጭ አገሮች ታሪክ ጋር በማጣቀስ ማብራሪያዎችን በመስጠት የቀረበ ቢሆንም እኔ ግን እጅግ በጣም አጠር ባለና እኔ እንደተረዳሁት አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

እኔ እንደተረዳሁት ስል እኔ እንደተረዳሁት እንጂ ክፍሉ እንደ አቋም ወይም እንደ ጋራ ስምምነት ያስተላለፈው እንዳልሆነ በቅድሚያ አንባቢያን እንዲገነዘቡልኝ እወዳለሁ ።

ከየ ድርጅቶቹ ተገንጥለው የወጡና ከወያኔ ጋር አብሮ መስራት ይቻላል በማለት ወይንም ለመስራት ፍላጎትን በማሳየት የወያኔን መልካም ፈቃድ በመጠባበቅ ላይ ያሉ በጠላትነት መፈረጅ ይኖርባቸዋል የሚለውን ክፍሉ የተወያየበትን ጽንሰ ሀሳብ በመጠኑ ለመዳሰስ እሞክራለሁ ።

በጠላትነት መፈረጅ አለባቸው የሚለው ክፍል ክርክሩን ሲያቀርብ በተለይ በደርግ ዘመን ከደርግ ጋር አብሮ መስራት ይቻላል በማለት ከኢሕአፓ አፈንግጦ የወጣው ክፍል እንደምሳሌነት በማቅረብ ክርክሩን ይጀምራል ፤ በዚያን ወቅት ከደርግ ጋር የወገነው አፈንጋጭ ክፍል ምን ያክል ትግሉን እንዳኮላሸና የትግል ጓደኞቹንም እንዳስጨፈጨፈ ፣ እንዳስጨረሰ በማስታወስ ዛሬም በተመሳሳይ ሁኔታ ከወያኔ ጋር መስራት ይቻላል ብሎ የተነሳው ቡድን ነገር ግን እራሱን የወያኔ ተቀዋሚ ብሎ የሚጠራው ልክ እንደ ደርግ ዘመኑ መንግስት ወያኔ ተቀብሎ ቢያስገባቸው ካለፉት ወደ ደርግ ከተቀላቀሉት አንጃዎች ተመሳሳይ ድርጊት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ በማስገንዘብ ፤ ካለፈው ተመክሮ ትምህርት መውሰድ እንደሚገባ ለማስረዳት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። እነዚህ ቡድኖች ለጊዜው ያልታጠቁና በአብዛኛው በውጪው ዓለም ያሉ ከመሆናቸው በቀር በለስ ቀንቷቸው ወያኔ እጁን ዘርግቶ ቢያስገባቸው ካለፈው የአንጃ ቡድን ያልተለዩ እንዲያውም በከፋ ሁኔታ በእውነተኛው የወያኔ ተቃዋሚነት የተሰለፉትን የቀድሞ ጓዶቻቸው ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ጥፋት ቀላል እንደማይሆን ታሪካዊ ማስረጃዎችን በማጣቀስ ለማስረዳት ሞክረዋል ።

ምንም እንኳን አሁን የታጠቁና በሕዝብ ላይ ጉዳት እያደረሱ ባይሆኑም አካሄዳቸውና ህልማቸውም ከተሳካ አዝማሚያቸው ወደዚያው እንደሚሆን በማስገንዘብ ፤ ጨምረውም ይህንን መሰል አካሄድ ባለፈው በደርግ ዘመን ያየነውን በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ላይ የደረሰውን እልቂት ሊያደርሱ ስለሚችሉ የጠላትነት ደረጃቸው ባሁኑ ይዘታቸው ከወያኔ ጋር ባያወዳድራቸውም ቅሉ ፣ ነገር ግን ጎዞአቸው ወደዚያው ስለሆነ ሊታመኑ የሚችሉ ቡድኖች

ባለመሆናቸው የወያኔ የችግር ጊዜ ደራሽ (የእሳት አደጋ ሰራተኛ) በመሆን የሕዝብን ወገን ከማስመታት ወደኋላ ስለማይሉ ከወያኔ በመለስ በጠላትነት ሊፈረጁ ይገባል በማለትና ሌሎችንም አሳማኝ ግንዛቤዎችን በማቅረብ ተከራክረውበታል ። በመጨመርም መማርና መመለስን ፤ ፍቃደኝነትን ካሳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅር ባይና ላለፈው ጥፋታቸው የማይወቅሳቸውና የማይከሳቸው እንደሆነም ለማስረዳት ሙከራ ተደርጓል ።

በተጨማሪም ጠላት ከተባለ መመታት አለባቸው ማለት ነው ወይ? ተብሎ ለተነሳውም ሃሳብ መልስ ሲሰጡ ፣ መመታት የሚኖርበት መሳርያ አንስቶ የሕዝብን ወገን የሚያደማና የሚገል እንጂ በስመ ጸረ ሕዝብ ነገር ግን መሳሪያ አንስቶ የሕዝብ ወገንን ያልገደለ መመታት አይኖርበትም በማለት ብዥታን ለማጥፋት ታላቅ ሙከራ ሲደረግ አስተውያለሁ ፣ ጨምረውም አሁን ላለው ስርአት በሙሉ ልብና ጽናት የሚደግፍ የስርአቱ ታማኝ አገልጋይ ነገር ግን መሳሪያ አንስቶ ሕዝብን የሚጨርስ ሳይሆን በመንግስት መዋቅር ስር ሆኖ የሚሰራ የወያኔን ጉዳይ ለማስፈጸም ደፋ ቀና የሚለው የሲቪሉ አካል የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን ሕዝብን ስላልጨፈጨፈ ያለው የግፈኛ ምሰሶ ሆኖ ቢያገለግልም ቅሉ ይህ የፋሽስት አገዛዝ በሚወድቅበት ወቅት እሱም መመታት እንደማይኖርበት ነገር ግን ከስርአቱ መውደም ጋር አብሮ ስለሚወድም ሊያሳስበን የማይገባ የህብረተሰብ ክፍል እንደሆነ ካለፈው የደርግ ዘመን ተመክሮ በማገናዘብ እንዲህ ሲሉ አቅርበውታል ።

ባለፈው የደርግ ሥርአት ታማኝ ሎሌ የነበሩና ሥርአቱ እድሜው እንዲራዘም ቀን ከሌት ሲዋትቱ የነበሩ ቡድኖች ፤ የደርግ ካድሬዎች ፣ በቀበሌና በየመስሪያ ቤቱ ተሰግስገው ሕብረተሰቡን ቁም ስቅሉን ሲያሳዩ የነበሩ በሙሉ መመታት አለባቸው ቢባል ኖሮ የደርግን ስርአት በሁለት እግሩ እንዲቆም ያደረጉት ግለሰቦች ቁጥር ቀላል እንዳልነበረና ከስርአቱም መምከን በኋላ የብዙ ሰዎች ደም በፈሰሰ ነበር ፤ ነገር ግን እነኚህ የስርአቱ አገልጋዮች ቢሆኑም ቅሉ መሳሪያ በማንሳት የሰው ሕይወት ስላላጠፉ የነሱም ህልውና ከስርአቱ መጥፋት ጋር አብሮ ስለሚጠፋ እነሱን መምታት አስፈላጊ እንዳልሆነ በሰፊው በማብራራት አላስፈላጊነቱን ለማስረዳት የቀድሞው የደርግ ስርአት አገልጋዮች የነበሩ ነገር ግን በሲቪል ማሕበሩ ውስጥ እንጂ መሳሪያ አንስተው ደም ያላፈሰሱ ይሄው እስከ ዛሬ በሐገራቸው ከሕብረተሰቡ ተቀላቅለው ነገር ግን የቆሰለች ጥንቸል ሆነው በሕብረተሰብ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያደርሱ ሆነው መቀመጣቸውን እንደ ማስረጃ በማድረግ ለማቅረብ ችለዋል ። አያይዘውም አሁን በጠላትነት የተፈረጁ ሆኖም ግን መሳሪያ አንስተው የሕዝብ ወገን ደም ያላፈሰሱ መመታት ባይኖርባቸውም ነገር ግን የጠላትነት ደረጃቸውን ዝቅ አድርጎ ወይንም ፍቆ ወደ ወዳጅ ካምፕ ያስገባቸዋል ማለትም እንዳልሆነ አስምረውበት አልፈዋል ።

እንዲያው የውይይቱ ብስለትና ይዘቱ ስላስደሰተኝ ፣ በአሲምባ የውይይት ክፍል ውስጥ ምን እየተወያዩ እንደሆነ ለማሳወቅ ፤ ለመድረኩም ያለኝን አድናቆት ለማበርከት እንጂ የውይይቱን ጠቅላላ ይዘት እቺ አጭር ጽሁፍ ትሸፍነዋለች በማለት እንዳልሆነ ላስገነዝብ እወዳለሁ ፤ እግረመንገዴንም ኢትዮጵያውያኖች መድረኩን በመቀላቀል የተቻላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚኖርባቸውም እያሳሰብኩ ። በሚቀጥለው ቅዳሜም እንዳለፈው ወይም የበለጠ ውይይት ሊኖር እንደሚችል ተስፋ በማድረግ በናፍቆት እጠባበቃለሁ እናንተም አያምልጣችሁ እላለሁ ::

ሕብረታችን ይጠንክር!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ድሉን ይቀዳጃል!!

ሥዩም ዋቅጅራ